» ከመኪናዎ ውስጥ ስርቆትን ለማስወገድ የተሻለው አማራጭ የሚሆነው፣ ዋጋ ያላቸውን ዕቃዎች ሁልጊዜ “ከእይታ መሰወር” ነው። የእጅ ስልኮችን፣ የሰነድ ቦርሳዎችን፣ ሻንጣዎችን ወይም ትናንሽ በኤሌክትሪክ የሚሰሩ መሳሪያዎችን (የግል የሙዚቃ ማጫወቻዎች፣ ዲጂታል እርዳታ መስጫዎች፣ ወዘተ...) በመኪና ውስጥ በግልጽ እይታ በጭራሽ አይተዉ። ይዘው ይውረዱ፣ ወይም ሁልጊዜ፣ በማንኛውም ጊዜ —በተሰወረ ቦታ ይቆልፉ!

» መኪናዎ ኮፈን ካለው ይጠቀሙበት። ዋጋ ያላቸው ዕቃዎችን በውስጡ ያስቀምጡ ወይም ከፊት የጓንቲ ማስቀመጫ (glove compartment) ውስጥ ቆልፈው ያስቀምጡ። ቁሳቁሶችን ፊት ለፊት በግልጽ እይታ ከመተው በመቀመጫ ስር መደበቅ የተሻለ ነው፤ ሆኖም፣ በጓንቲ ማስቀመጫ ወይም በኮፈን ውስጥ መቆለፍ እጅግ በጣም የተሻለ መከላከያ ነው።

» በተለይ በበዓል ወቅት ወይም ግብይት በሚያደጉበት በሌላ ጊዜ ጥቅሎችን በኮፈን ውስጥ ይክተቱ፣ በተሳፋሪ መቀመጫ ላይ ወይም በመኪናው ወለሎች ላይ አይተዉ።

» ከመኪናው ጋር የተሰራና በዚያ መኪና ጋር ብቻ የሚሰራውን የመኪና ሬዲዮ ወይም ሌላ የሙዚቃ ማጫወቻዎች ይጠቀሙ። ይህ የመሰረቅ ስጋትን ይቀንሳል።

» ከተቻለ የሙዚቃ ማጫወቻውን ነቅለው ይዘው ይውረዱ፤ ወይም በኮፈኑ ውስጥ ይቆልፉ። ይህንኑ ዘዴ ለሲዲ እና ለቴፕ ማጫወቻ መጠቀምን አይርሱ።

» በተጨማሪም፣ ሁልጊዜ — የመኪናዎን በሮችና መስኮቶች ይቆልፉ!

## መኪና ነጠቃ (Carjacking)

በኃይል መኪና ነጠቃ ወንጀል በተለየ መልኩ አስፈሪ ሆኖ ቢገኝም፣ እራስዎን ለመጠበቅ የሚያደርጓቸው አንዳንድ ነገሮች አሉ። ሁልጊዜ አካባቢዎን በደንብ ያጢኑ፣ በርዎን ይቆልፉ፣ መስኮትዎን ይዝጉ፣ በመካከለኛው የመኪና መንገድ መስመር ይንዱ፣ ፍርሀት ከተሰማዎት ለፖሊስ ይደውሉ። ለተጨማሪ አስተያየቶች፣ “Avoiding Becoming a Victim of Carjacking” የሚለውን ተከታታይ የተለየ የመግለጫ ጽሁፎችን ይመልከቱ።

### *አድራሻ*

MPD Auto Theft Unit
300 Indiana Avenue, NW
Washington, DC 20001
(202) 724-1360

### ተጨማሪ የደህንነት ጥቆማዎችን ያግኙ

በየዕለት ኑሮዎ ከወንጀል ሊጠብቁዎት የሚችሉ ሌሎች ጥቆማዎችን ለማግኘት፤ ከዚህ በተከታታይነት የሚገኙትን መጽሔቶችን በድህረ-ገፃችን **www.mpdc.dc.gov/safety** ይመልከቱ። ወይም የአካባቢዎን የፖሊስ ጣቢያ ይጎብኙ። በአቅራቢያዎ ያለውን ለማግኘት **www.mpdc.dc.gov/districts** ይጎብኙ።

## ተሳታፊ ይሁኑ!

ማንኛውም ግለሰብ ወይም ድርጅት ብቻውን በመሥራት ወንጀልን መከላከል አይችልም። ፖሊሶችና ዜጎት በትብብር መሥራት ያስፈልጋቸዋል። የኮሎምብያ ዲስትሪክት የማህበረሰብ ጥበቃ ዕቅድ፣ ፖሊሶችና ማህበረሰቡ ወንጀልን ለመከላከልና ደህንነቱ የተጠበቀ አካባቢዎችን ለመገንባት አብሮ ለመሥራት የተለያዩ መንገዶችን ያቀርባል። እነኝህም በማህበረሰብዎ መደበኛ የፖሊስ አገልግሎት የአካባቢ ስብሰባዎችን፣ የዜጎች ጥበቃዎችና ሌሎችንም ያካትታል። ስለአካባቢዎ የማህበረሰብ የፖሊስ እንቅስቃሴዎች የበለጠ ለመረዳት፣ የአካባቢውን የፖሊስ ዲስትሪክትን በሚከተለው ይደውሉ፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1ኛ ዲስትሪክት | ዋና መ/ቤት: | **(202) 698-0555** | TTY: **727-8506** |
| | ቅርንጫፍ መ/ቤት: | **(202) 698-0068** | TTY: **543-2352** |
| 2ኛ ዲስትሪክት | ዋና መ/ቤት: | **(202) 715-7300** | TTY: **364-3961** |
| 3ኛ ዲስትሪክት | ዋና መ/ቤት: | **(202) 673-6815** | TTY: **518-0008** |
| 4ኛ ዲስትሪክት | ዋና መ/ቤት: | **(202) 715-7400** | TTY: **722-1791** |
| | *ቅርንጫፍ መ/ቤት:* | **(202) 576-8222** | TTY: **576-9640** |
| 5ኛ ዲስትሪክት | ዋና መ/ቤት: | **(202) 698-0150** | TTY: **727-5437** |
| 6ኛ ዲስትሪክት | ዋና መ/ቤት: | **(202) 698-0880** | TTY: **398-5397** |
| | *ቅርንጫፍ መ/ቤት:* | **(202) 698-2088** | TTY: **281-3945** |
| 7ኛ ዲስትሪክት | ዋና መ/ቤት: | **(202) 698-1500** | TTY: **889-3574** |

## ስለ ወንጀል የሚያውቁት አለን? በሚስጥር አይይያዙት

ከፖሊስ ጋር ለማጋራት የሚፈልጉት ጠቃሚ መረጃ ካለዎት፣ በስም አልባ የወንጀለኛ መጠቆሚያ መስመር እና ቴክስት መጠቆሚያ መስመር ለMPD አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ማንነትዎን ሳያሳውቁ መስጠት ይችላሉ። 24 ሰዓት በቀን፣ ሰባት ቀናት በሳምንት በ**(202)727-9099** ይደውሉ ወይም በ**50411** ቴክስት (text) ያድርጉ። ከሰጡት መረጃ በስተቀር ስምዎን አንጠቀምም። የሚሰጡት መረጃ የገንዘብ ሽልማት ሊያስገኝልዎት ይችላል። ለተጨማሪ መረጃዎች፣ **www.mpdc.dc.gov/tipline** ይመልከቱ።

GIVE 5-0 THE 4-1-1
Have information for police?
**CALL (202) 727-9099**
**TEXT TO 50411**

የኮሎምብያ ዲስትሪክት መንግሥት
የሜትሮፖሊታን ፖሊስ መምሪያ
300 Indiana Avenue, NW
Washington, DC 20001

ለ ደ ህ ን ነ ት ዎ



# መኪናዎን ከሌብነት እና ከመነካካት መከላከል

*መኪናዎን ከመበዝበዝ፣ ከመሰበርና ከመሰረቅ የመከላከል ጥቆማ*

# እራስዎን ከችግር ያድኑ።

**በኮሎምብያ ዲስትሪክት ውስጥ በየቀኑ ወደ 18 የሚጠጉ መኪናዎች ይሰረቃሉ። እነኝህ የሚሰረቁ፣ ቫኖች፣ መኪናዎች፣ የሞተርብስክሌቶች እና ትራኮች፣ ለስርቆቱ ሰለባ የሆነውን ሰው ጊዜና ገንዘብ እንዲሁም የኢንሹራንስ ክፍያዎች እንዲጨምር ያደርጋሉ። አብዛኛውን ጊዜ የተሰረቁ መኪናዎች ሌላ ወንጀል ለመስራት ጥቅም ላይ ይውላሉ።**

መኪናዎ ለዚህ አደጋ ዒላማ እንዳይሆን ለማድረግ አንዳንድ ቀላል ቅድመ ሁኔታዎችን በመውሰድ እራስዎንና ቤተሰብዎን ከብዙ መሳቀቅ፣ መጨነቅ እና የየእለት ህይወት ከመጨናገፍ ማዳን ይችላሉ። መኪናዎ - እና በውስጡ የሚገኙትን ዋጋ ያላቸውን ዕቃዎች - ለሌቦች እንዳይማርክ ለማድረግ የሚከተሉት አንዳንድ  እርምጃዎች መውሰድ ይችላሉ።

## የተለመደ የተፈጥሮ ግንዛቤን ልምድ ማድረግ

ምንም ዓይነት የሌባ መከላከያ መሣሪያ ቢጠቀሙም፣ ያልተቆለፈ እና ቁልፉ ሞተር ማስነሻው ላይ የተተወን መኪና ማንኛውንም ሌባ በግልጽ የሚጋብዝ ነው። ከሌቦች ለመከላከል የተለመደ  የተፈጥሮ ግንዛቤን ልምድ በማድረግ መከላከል፣ ቀላልና ወጪ የሌለው የሌብነት መከላከያ ዘዴ ነው።

“ለአንድ ደቂቃ ብቻ” እንኳ ቢያቆሙ፣ መኪናዎን ሁልጊዜ መቆለፍ ይገባዎታል።  የሚከተሉትን ያድርጉ፡

» ቁልፍዎን ከሞተር ማስነሻው ላይ ማንሳት

» ሁሉንም በሮች መቆለፍ

» ሁሉንም መስኮቶች መዝጋት

» ደህና ብርሃን ባለበት አካባቢ ማቆም

» ወደመኖሪያ ቤትዎ፣ ወደሱቆች ወይም ሌላ ቦታ በችኮላ ሲሄዱ የመኪናውን ሞተር ሳያጠፉና መኪናውን ሳይቆልፉ በፍጹም አለመሄድ።

## የዕይታ ወይም የማዳመጫ መከላከያዎችን መጠቀም

የእይታ ወይም የማዳመጫ መሳሪያ ለሌቦች መኪናዎ መከላከያ እንደተደረገለት ይጠቁማቸዋል። የታወቁ መሳሪያዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ፣

» **ድምፅ የሚያሰሙ ደወሎች** በአጠቃላይ የእንቅስቃሴ ወይም እስከ 120-ዲሲብል ጩኸት ያለው ጠቋሚ ደወል አላቸው።  ደወሉ በራሱ የማጥፋት ብቃት ያለው መሆን አለበት።

» **የመሪ መቆለፊያ መሣሪያዎች** መሪውን ከመዞር ያግደዋል።

» **የመሪ ቋሚ መቆለፊያ መሣሪያዎች** ሌቦች መኪናውን ያለቁልፍ ከማስነሳት ያግዱታል።  አንዳንድ መቆለፊያዎች በቋሚነት የሚተከሉ ሲሆን፣ ሌሎቹ ደግሞ በየጊዜው ማስነሳት ይኖርባቸዋል።

» **የሌባ መከላከያ ታርጋዎች** መኪናዎቹ  በደወል ወይም በሌላ የሌባ መከላከያ መሣሪያ ጥበቃ የተደረገላቸው መሆኑን ለሌቦች በእይታ ብቻ ማስጠንቀቂያ ይሰጣል።

» **የጎማ መቆለፊያዎች** በርካታ የፖሊስ መምሪያዎች ከሚጠቀሙባቸው ጋር ተመሳሳይነት ያለው ክብ የጎማ መቆለፊያ መኪናውን ከመነዳት ይከለክለዋል።

» **መስታወት ላይ የመቅረጽ ጥበብ።** የመኪናው መለያ ቁጥር (VIN)



በመኪናው መስኮት ላይ ተቀርጾ ከሆነ፣ ሌቦቹ መኪናውን ወይም የመኪናውን አካሎች ለመሸጥ ያስቸግራቸዋል።

## የመከታተያ ዘዴ ወይም መኪናን ከእንቅስቃሴ መግቻ መጠቀም

መኪናው መሰረቁን ሪፖርት በሚደረግበት ጊዜ ለፖሊስ ወይም ለቁጥጥር ጣቢያው ምልክት የሚያስተላልፍ የመከታተያ ዘዴ ነው። የመከታተያ ዘዴዎቹ፣ ለባለሥልጣናቱ የተሰረቁ ተሽከርካሪዎችን እንዲያገኙ ፍቱን የሆኑ ረዳቶች ናቸው።

የመኪና እንቅስቃሴ መግቻዎች ሌቦች ተሽከረካሪዎችን ያለቁልፍ ከማስነሳት ያግዳሉ። አንዳንድ የኤሌክትሪክ መሣሪያዎች በማስነሻው ቁልፍ ውስጥ የኮምፒውተር ቺፕ አሏቸው። ሌሎች መሣሪያዎች ደግሞ የተደበቀ ማብሪያና መጥፊያ ወይም ቁልፍ እንዲሰራ ካልተደረገ በቀር ኤሌክትሪክ ወይም ነዳጅ ወደ ሞተሩ እንዳያልፍ ይከለክላሉ። የታወቁ ባለሶስት-ደረጃ መሳሪያዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡

» ስማርት ቁልፎች (Smart keys)፣ ልዩ ኮድ ያለው የኮምፒውተር ቺፕ ወይም ራዲዮ ሞገድ አላቸው። ከትክክለኛው ቁልፍ በስተቀር የመኪናው ሞተር አይነሳም።

» ፊውዝ (Fuse) ማቋረጫዎች።

» ማብሪያና ማጥፊያዎችን የሚያቆም — የተደበቀ ማብሪያና ማጥፊያ እንዲሰራ እስከሚደረግ ድረስ የኤሌክትሪክ ስርጭት ወይም ነዳጅ ወደ ሞተሩ እንዳይሄድ ያደርጋል።

» ማስነሻ፣ ሞተር እና ነዳጅ እንዳይሰራ የሚያደርጉ

## መኪና ሲገዙ ጥንቃቄ ያድርጉ

ያገለገሉ —ወይም— አዲስ መኪና ሲገዙ ጠንቃቃ መሆን፣ ወደፊት ሊገጥምዎ ከሚችል አደገኛ የሆነ የራስ ምታት ወይም ጭንቀት ሊጠብቅዎ ይችላል። ከመጭበርበር የሚከተሉት ሊያድኑዎት ይችላሉ፣

» በሹፌሩ የፊት መስታወት በኩል የሚገኘውን የመኪና መለያ ቁጥር (VIN) ተለጣፊ፣ እንዳልተነካካ **አተኩረው በቅርበት ይመልከቱ።**

» የመኪናውን ታይትል (title) ወይም ሮዝ ተቆራጭ ሰነድ (pink slip) **በአካል ቀርቦ** ሳያዩ ያገለገለ መኪና **በጭራሽ** አይግዙ። የመኪናውን VIN፣ ከታይትሉ፣ የምዝገባ ወረቀቶችና በሹፌሩ የጎን በር ካለው የፌደራል ማረጋገጫ ተለጣፊ ላይ ካለው ቁጥር ጋር ደጋግመው ያመሳክሩ።

» መኪናውን የሚሸጥልዎን ሰው **መታወቂያ እንዲያሳይዎ ይጠይቁ።** ስሙን/ሟን፣ አድራሻ፣ የስልክ ቁጥር፣ የመንጃ ፈቃድ ቁጥር ይመዝግቡ። በመኪናው ባለቤት የተሰጠዎትን የስልክ ቁጥር ይደውሉ። አብዛኛውን ጊዜ በማጭበርበር የተካኑ በክፍያ የሚሰሩ የሕዝብ ስልክ ቁጥሮችን ይሰጣሉ።

ያገለገለ መኪና መግዛት የሚያስቡ ከሆነ፣ የመኪናውን VIN በኮምፒውተራቸው በማስገባት በትንሽ ክፍያ የመኪናውን ጠቅላላ ታሪክ ማረጋገጥ የሚችሉ በርካታ ኩባንያዎች አሉ። ኩባንያዎቹን በድህረ ገጽ ላይ “Vehicle History Reports” ብለው ቢፈልጉ ያገኟቸዋል።

## *የመለያ ቁጥሮች (VIN) የማጭበርበሪያ ዓይነቶች*

የVIN ማጭበርበሪያ የመኪና መለያ ቁጥሮች (VINs) ተመሳሳይ ስሪት እና ሞዴሎች ያሏቸውን መኪናዎች ለመለየት የሚያገለግሉ ተከታታይ ቁጥሮች ናቸው። እያንዳንዱ መኪና የተለየ VIN አለው። የVIN መለጠፊያው በመኪናው የፊት ዳሽቦርድ ላይ የሚገኝና በመኪናው የፊት መስታወት በኩል የሚታይ ነው።




**VIN መቀየር:** ሌቦች የተሰረቀን መኪና መለያን ለመደበቅ VIN ቁጥሩን በመቀያየር ይጠቀማሉ። በተሰረቀው መኪና ላይ ያለውን VIN በስርቆት ያልተመዘገበ ሌላ VIN ይተካሉ። ሌባው የተሰረቀውን መኪና ለማይጠራጠር ደንበኛ ለመሸጥ ይሞክራል።

**ከጥቅም ውጪ የሆነን መቀየር:** በከባድ ሁኔታ የተጎዳ መኪና፣ የተቃጠለ ወይም የተገነጣጠለ እና እንደገና ለመሰራት ብቃት የሌለው “Salvaged” ይባላል። ሌቦች ታይትል እና VIN ለማግኘት ብቻ እነኝህን የተጣሉ መኪናዎች ይገዛሉ። ቀጥሎም፣ አንድ ዓይነት ስሪትና ሞዴል ያለውን መኪና ሰርቀው የVIN መለጠፊያውን ይቀይራሉ።

## የመኪና ውስጥ ስርቆት

ከተለመዱ የስርቆት ዓይነቶች አንዱ ከመኪና ውስጥ ዋጋ ያላቸውን ዕቃዎች መስረቅ ነው። ከመኪና ውስጥ ስርቆት የወንጀል ክፍተት ሲሆን፣ ይህን ክፍተት ከተከላከሉት ማስወገድ የሚቻል ነው። በአጠቃላይ ሌቦች በግልጽ ሁኔታ የተቀመጡ ዋጋ ያላቸው ዕቃዎችን ካላዩ ተሽከርካሪውን ለመስበር ጊዜ አያጠፉም።